Kartläggningsmaterial för nyanlända elever

AMHARISKA

# Uppgifter B Textpaket
## Litteracitet

1 Steg 2 3

## Elever som läser och skriver



Skolverket



# Innehåll

**Inledning ... 3**

**Textpaket 1**

Lejonet och räven ... 5

En karta över en ö ... 7

Skorpionen ... 9

**Textpaket 2**

Skorpionen ... 12

Den giriga mannen ... 14

Potatischips ... 16

**Textpaket 3**

Skorpionen ... 19

Potatischips ... 21

Sömn ... 23

Mjölk ... 25

Världens städer ... 27

**Litteratur- och bildförteckning ... 29**

Skolverket och andra rättighetsinnehavare har upphovsrätt till materialet och delar som ingår i materialet. Materialet får inte mångfaldigas eller sparas på dator i annat syfte än för att genomföra en bedömning av nyanlända elevers kunskaper.



# Inledning

Detta häfte innehåller underlag för *Uppgifter B – Textpaket*. Uppgifterna använder du tillsammans med *Samtals- och dokumentationsunderlag B* och *Bedömningsunderlag för Uppgifter B.*

Instruktionerna för hur du genomför uppgifterna finns i *Samtals- och dokumentationsunderlag B.*

Dokumentera elevens svar på uppgifterna i bedömningsunderlagen. Var uppmärksam på att svarsrutorna för ”Ja” och ”Nej” kommer i en annan ordning på elevens svarsblad när språket har läsriktningen höger–vänster.

Varje uppgift består av två blad – en text och elevens svarsblad med läsförståelsefrågor. Information om hur du väljer uppgifter till eleven finns i lärarhandledningen (se s. 6–7). Skriv ut uppgifterna i färg och enkelsidigt så att eleven kan se texten och frågorna samtidigt.

Ge gärna tolken kopior av uppgifterna du har valt, både på svenska och på elevens språk.

## Om översättningen

Översättningen använder den standard som enligt lag (1994) är nationellt språk i Etiopien. De allra flesta användare av amhariska är flerspråkiga och behärskar andra språk som förekommer i det geografiska närområdet. Amhariska är officiellt skol- och undervisningsspråk inom de obligatoriska skolformerna i de flesta regioner i Etiopien. Det förekommer dock andra regionala undervisningsspråk. Amhariska använder ge’ez-skriften, som omfattar 180–250 olika tecken. Skriftsystemet är både ljudavbildande och stavelseåtergivande. Läs- och skrivriktningen är från vänster till höger.

## Anpassning av uppgifter för elever med funktionsnedsättning

Om du läser upp eller spelar in uppgifter för elever med svår synnedsättning behöver du anpassa uppgifter som innehåller bilder eller figurer. Kontakta en speciallärare eller specialpedagog om det behövs.

### Textpaket 1

- Text 1. Lejonet och räven. Beskriv innehållet i bilden.
- Text 2. En karta över en ö. Uppgiften stryks.
- Text 3. Skorpionen. Beskriv skorpionen i bilden. (Ingår även i textpaket 2 och 3)

### Textpaket 2

- Text 3. Potatischips. Använd riktiga potatischips. (Ingår även i textpaket 3)

### Textpaket 3

- Text 3. Sömn. Figuren kan strykas. Frågorna 3 och 4 som bygger på information i figuren stryks.
- Text 5. Världens städer. Diagrammet kan strykas. Frågorna 2 och 4 som bygger på information i diagrammet stryks.

Läs mer i *Anpassning för elever med funktionsnedsättning.*

# Textpaket 1



# ኣንበሳውና ቀበሮዋ

ኣንበሳው ዋሻው ውስጥ ጋደም ብሎ ነበር።
እዛም ቀንና ሌሊት ተጋድሞ ነበር።
ከሱም ትንሽ ደከም ያለ የማቃሳት ድምጽ ይሰማ ነበር።
እንስሶችም ”ታሟል” ብለው ኣሰቡና ደግሞም ኣዘኑለት።
እነሱም ትናንሽ ስጦታ በመያዝ ወደ ኣንበሳው ዋሻ ውስጥ መግባት ጀመሩ።

ቀበሮዋ ግን ውስጥ ኣልገባችም።
ኣንበሳው በለስላሳ ድምጽ ጠየቃት።
”ወዳጄ ፣ ኣንችስ ለምንድነው የማትመጭው? ሌሎች ሁሉ እዚህ ነበሩ።”

”ልመጣ ኣስቤ ነበር፣” ኣለች ቀበሮዋ። ”ነገር ግን የእግር ምልክቶችን ኣይቼ ፈራሁኝ። ሁሉም የእግር ምልክቶች ወደ ዋሻህ ውስጥ ገብቶኣል። ወደ ውጭ የወጣ የእግር ምልክት ግን የለም። ስለዚህ እኔ ውጭ ብቆይ ይሻለኛል።”





K. Aronsson & S. Ottosson, *Min läsebok*. 1993. Bearbetad. Bild: I-K. Eriksson.

# ጥያቄዎች ስለ ”አንበሳውና ቀበሮዋ”።


## የሚከተሉትን ጥያቄዎች አዎ ወይም አይደለም በማለት መልስ፡፡

| | | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | አንበሳው ሁልጊዜ ነው ወይ ዋሻው ውስጥ የነበረው? | ☐ | ☐ |
| 2. | ቀበሮዋ ወደ አንበሳው ሄዳ ነበረች ወይ? | ☐ | ☐ |
| 3. | ቀበሮዋ ለአንበሳው ስጦታ ሰጥታ ነበረች ወይ? | ☐ | ☐ |
| 4. | አንበሳው ሌሎቹን እንስሶች በልቶአቸዋል ወይ? | ☐ | ☐ |

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ፡፡

5. ጽሑፉ ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል አሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?
6. አንበሳው ታሞ የነበረ ይመስልሃል? እንዴት እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ?
7. ቀበሮዋ ከሌሎቹ እንስሶች ብልህ ነበረች ወይ? እንዴት እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ?
8. ከዚህ ተረት ሰዎች የሆነ ነገር መማር የሚችሉ ይመስልሃል ወይ? እንዴት እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ?

# የአንድ ደሴት ካርታ ።





Anpassad med tillstånd från IEA. © 1990.

# ጥያቄዎች ስለ ” ደሴት ካርታ”።

ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት ኣድርግ። ኣንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።

**1. ከነኝህ ቦታዎች ለወደቡ ቅርብ የሆነ የትኛው ነው?**

A ☐ ከተማው
B ☐ ሃይቁ
C ☐ የእርሻ ቦታው

**2. ከነኝህ ቦታዎች ለከተማው በስተሰሜን በኩል ያለው የትኛው ነው?**

A ☐ የኣውሮፕላኑ ማረፍያው
B ☐ ጫካው
C ☐ የእርሻ ቦታው

**3. ከከተማው ወደ ሃይቁ ኣቅጣጫ ስትሄድ፣ በየትኛው በኩል ነው የምትሄደው?**

A ☐ በሰሜን
B ☐ በምዕራብ
C ☐ በምስራቅ

**4. ራስህን በደሴት ውስጥ እየሄድኩ ነው ብለህ ኣስብ። መመሪያዎቹን ተከተል።**

1. ከመንደሩ ጀምር።
2. የወደቡን መንገድ ተከትለህ ሂድ።
3. ሁለተኛው መስቀለኛ መንገዱ ጋር ስትደርስ ወደ ግራ ታጠፍ።
4. መንገዱ እስኪያልቅ ድረስ ቀጥል።
5. ኣሁን የት ቦታ ነው ያለህው?

A ☐ የእርሻ ቦታው
B ☐ ከተማው።
C ☐ ወደቡ።

# ጊንጥ – የሸረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው

በሞቃታ ቦታዎች በሚገኙ ግድግዳዎች ውስጥ በሚፈጠር ትናንሽ ቀዳዳዎች እና ድንጋዮች መካከል ጣታችሁን መክተት ኣይመከርም። በተጨማሪም ባዶውን ለረጅም ጊዜ የቆየ ጫማ ማራገፍ ይገባል። ምናልባት ኣሁን ባዶውን ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ጊንጦች ብርሃን ኣይወዱም። ስለዚህም ነው በቀዳዳና ጨለም ባሉ ቦታዎች ተጣብቀውና ተኝተው ቀኑን የሚያሳልፉት። ጊንጦች በመላው ዓለም በሞቃት ኣገሮች ይኖራሉ፡ ግን ብዙውን ጊዜ ኣይታዩም።

## ያደኑትን ነፍሳት ወግቶ መግደል

ጊንጦች በእርግጥ መርዛማ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን ኣብዛኛዎች ዝርያዎች ለኛ ለሰው ልጆች ለሞት የሚያበቁን ባይሆኑም፣ እነሱም እንደየ ዝርያቸው ቁመታቸው ከኣንድ እስከ ሃያ ሴንቲሜትር ይሆናሉ። ነገር ግን ሁሉም ጊንጦች መርዛማ የሆነ መንደፍያ ጭራቸው ጫፍ ላይ ኣላቸው። ኣንድ ጊንጥ ያደነውን ነፍሳት ለመግደል ሲል ጭራውን ወደ ጀርባው በማዞር ያንን ያደነውን ነፍሳት በጥፍሩ ኣጥብቆ ይዞ ይወጋዋል። ኣንድ የፈራ ጊንጥ መንደፍያውን ወደ ጠላቱ በማመልከት ዙርያውን በፍጥነት ይሽከረከራል።

ጊንጦች ትላልቅ ሸረሪቶችንና ሌሎች ትናንሽ ነፍሳቶችን በሌሊት ያድናሉ። እነሱም በጥፍራቸው በመዳሰስ ያደኑትን ነፍሳት ቀርቅረው በመያዝ በዛ መርዛማ መንደፍያቸው ኣድርገው ይገድሉታል።



*ጊንጥ*



K. Åström, *Boken om världen.* 2001. Fotografi Wikimedia Commons.

# ጥያቄዎች ስለ ”ጊንጥ – የሸረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው”

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ኣዎ ወይም ኣይደለም በማለት መልስ።**

| | | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|---|
| **1.** | ጊንጦች ጨለማ ይወዳሉ? | ☐ | ☐ |
| **2.** | ሁሉም ጊንጦች ሰዎችን ሊገድሉ ይችላሉ? | ☐ | ☐ |
| **3.** | ሁሉም የጊንጥ ዝርያዎች እኩል ናቸው? | ☐ | ☐ |
| **4.** | ጊንጦች በጥፍራቸው ነው ወይ ያደኑትን የሚይዙት? | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

5. ጽሑፉን ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል ኣሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?

6. ከዚህ ስለ ጊንጦች ከተጻፈው ጽሑፍ ውስጥ ሰው ጫማውን ማራገፍ ኣለበት ይላል፡ ይሄ ለምን መደረግ ያለበት ይመስልሃል? ለምን እንደሱ እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ ወይ?

# Textpaket 2



# ጊንጥ – የሸረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው

በሞቃታ ቦታዎች በሚገኙ ግድግዳዎች ውስጥ በሚፈጠር ትናንሽ ቀዳዳዎች እና ድንጋዮች መካከል ጣታችሁን መክተት ኣይመከርም። በተጨማሪም ባዶውን ለረጅም ጊዜ የቆየ ጫማ ማራገፍ ይገባል። ምናልባት ኣሁን ባዶውን ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ጊንጦች ብርሃን ኣይወዱም። ስለዚህም ነው በቀዳዳና ጨለም ባሉ ቦታዎች ተጣብቀውና ተኝተው ቀኑን የሚያሳልፉት። ጊንጦች በመላው ዓለም በሞቃት ኣገሮች ይኖራሉ፡ ግን ብዙውን ጊዜ ኣይታዩም።

## ያደኑትን ነፍሳት ወግቶ መግደል

ጊንጦች በእርግጥ መርዛማ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን ኣብዛኛዎች ዝርያዎች ለኛ ለሰው ልጆች ለሞት የሚያበቁን ባይሆኑም፣ እነሱም እንደየ ዝርያቸው ቁመታቸው ከኣንድ እስከ ሃያ ሴንቲሜትር ይሆናሉ። ነገር ግን ሁሉም ጊንጦች መርዛማ የሆነ መንደፍያ ጭራቸው ጫፍ ላይ ኣላቸው። ኣንድ ጊንጥ ያደነውን ነፍሳት ለመግደል ሲል ጭራውን ወደ ጀርባው በማዞር ያንን ያደነውን ነፍሳት በጥፍሩ ኣጥብቆ ይዞ ይወጋዋል። ኣንድ የፈራ ጊንጥ መንደፍያውን ወደ ጠላቱ በማመልከት ዙርያውን በፍጥነት ይሽከረከራል።

ጊንጦች ትላልቅ ሸረሪቶችንና ሌሎች ትናንሽ ነፍሳቶችን በሌሊት ያድናሉ። እነሱም በጥፍራቸው በመዳሰስ ያደኑትን ነፍሳት ቀርቅረው በመያዝ በዛ መርዛማ መንደፍያቸው ኣድርገው ይገድሉታል።



*ጊንጥ*



K. Åström, *Boken om världen.* 2001. Fotografi Wikimedia Commons.

# ጥያቄዎች ስለ "ጊንጥ – የሸረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው"

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ኣዎ ወይም ኣይደለም በማለት መልስ።**

| | | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|---|
| **1.** | ጊንጦች ጨለማ ይወዳሉ? | ☐ | ☐ |
| **2.** | ሁሉም ጊንጦች ሰዎችን ሊገድሉ ይችላሉ? | ☐ | ☐ |
| **3.** | ሁሉም የጊንጥ ዝርያዎች እኩል ናቸው? | ☐ | ☐ |
| **4.** | ጊንጦች በጥፍራቸው ነው ወይ ያደኑትን የሚይዙት? | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

5. ጽሑፉን ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል ኣሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?

6. ከዚህ ስለ ጊንጦች ከተጻፈው ጽሑፍ ውስጥ ሰው ጫማውን ማራገፍ ኣለበት ይላል፡ ይሄ ለምን መደረግ ያለበት ይመስልሃል? ለምን እንደሱ እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ ወይ?

# ስስታሙ ሰውዬ።

ኣንድ ስስታም ሰው የነበረውን ሃብት ሁሉ ሸጦ፣ ያገኘውን የወርቅ ገንዘብ ኣቅልጦ ወደ ኣንድ ድቡልቡል ወርቅ ቀየረው። ይሄን ድቡልቡል ወርቅ እዛው ቤቱ ግቢ ውስጥ የነበርው ዛፍ ስር ቀበረው። በየቀኑ ዛፉ ድረስ እየሄደ ወርቁ እንዳይጠፋበት ይጠብቅ ጀመር። ኣንድ ቀን ከጐሮቤቶቹ ኣንዱ ኣየውና፣ ወዲያው ምን ይሰራ እንደነበር ነቃበት። ስስታሙ ሰውዬ ከቦታው ከሄደ በኋላ፣ ጐረቤቱ ጥሩ ኣጋጣሚ ኣግኝቶ ድቡልቡሉን ወርቅ ከተቀበረበት ቦታ ኣውጥቶ ይዞት ሄደ።

በማግስቱ ስስታሙ ሰውዬ ወርቁን ለማየት ሲሄድ፣ ኣንድ ጉድጓድ ኣገኘ። ያኔ ከከባድ ሃዘን የተነሳ ጸጉሩን መንጨት ጀመረ። ኣንደ ኣጋጣሚ በዛ በኩል ትሄድ የነበረች ጓደኛው ምን እንደሆነ ጠየቀችው። ስስታሙ ሰውዬ ምን አንደሆነ ነገራት።

”እንዴ! ሌላ ነገር ኣይደለም? ኣለችው ጓደኛው፣ ታዲያ በጣም የምታዝንበት ምክንያት እኮ የለህም፣ ምክንያቱ ወርቁ በእርግጥ ያንተ ኣልነበረም። በምትኩ ኣንድ ድንጋይ በጉድጓዱ ውስጥ ኣስገባና፣ ይሄን ድንጋይ ድቡልቡል ወርቅ ነው ብለህ ራስህን ኣሳምን። ከዚህ በኋላ ትልቅ ደስታና ጥቅም ታገኛለህ”።



Efter Aisopos. Bearbetad och översatt från svenska.

# ጥያቄዎች ስለ ”ስስታሙ ሰውዬ”

**ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት ኣድርግ። ኣንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።**

1. **ስስታሙ ሰውዬ ድቡልቡሉን ወርቅ እንዴት ኣገኘው?**

ሀ ☐ የገዛው ከጐረቤቱ ነው።.
ለ ☐ ከወርቅ ገንዘብ የሰራው ነው ።.
ሐ ☐ ከቤቱ ግቢ ውስጥ ኣገኘው።

2. **ስስታሙ ሰውዬ በየቀኑ ዛፉ ድረስ የሚሄደው ለምንድነው?**

ሀ ☐ ተጨማሪ ወርቅ ለመቅበር።
ለ ☐ የቀበረው ወርቅ ለማውጣት።
ሐ ☐ ወርቁን ለመጠበቅ ።

3. **ከዚሁ ታሪክ ምን መማር ይቻላል?**

ሀ ☐ ኣንድ ሰው ካለው ሃብት ሌላውን መርዳት እንዳለበት።
ለ ☐ ኣንድ ሰው ሃብቱ ጥቅም ላይ ሲውል ደስታ ይሰመዋል።
ሐ ☐ ኣንድ ሰው ሁሉ ጊዜ የጎረቤቶቹንና የጓደኞቹን ምክር መስማት ኣለበት።

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።.

4. ጽሑፉ ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል ኣሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?

5. ስስታሙ ሰውዬ ንብረቱን የሸጠበት ምክንያት ለምን ይመስለሃል? እንዴት እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ?

6. ጓደኛው ”በምትኩ ጉድጓዱ ውስጥ ድንጋይ ቢቀበር ያው ኣንድ ነው” ስትል ለምን ይመስለሃል? እንዴት እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ?

# ደረቅ የድንች ጥብስ



*ደረቅ የድንች ጥብስ*

ደረቅ የድንች ጥብስ በስስ ተከትፎ በዘይት ከተጠበሰ ድንች ሲሆን፣ ይሄም በ1800 ክፍለ ዘመን በጣም ከተወያዩበት ፈጠራዎች ኣንዱ ነው። ስለዚህም ለመጀመርያ ጊዜ ማን እንደፈጠረውና መቼ መሸጥ እንደተጀመረ ብዙ ታሪኮች ይወራሉ። ከነዚህ ታሪኮች ውስጥ እውነተኛ ይዞታ ያለውን ታሪክ ማግኘት ከባድ ሲሆን እንድያውም የማይቻል ነው።

ከዚህ ሁሉ በብዛት ከተወራው ታሪክ ስለ ምግብ ኣብሳዩ ጆርጅ ክሩም የተባለ ነበር። ነሓሴ 24 1853 ክሩም ለኣንድ ያልተደሰተ ደንበኛው ለማርካት ሞከረ። ስስ ኣድርጎ የቆራረጠውን ድንች በመጥበስ፣ ውጠቱ ላይ ደግሞ ጨው ነሰነሰበት፣ እንደ ውጤቱ ደግሞ ያ ደንበኛው ካለመደሰት ወደ በጣም የመደሰት ሁኔታ ተቀየረ። ይሄ ታሪክ ሃቀኛ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሌሎች ምግብ ኣብሳዮች በዚያ ዘመን ተመሳሳይ ሃሳብ ያስቡ እንደነበረ ሊታወቅ ተችሎኣል። በኣሜሪካ ብቻ በተመሳሳይ በኣንድ ሁለት የምግብ ኣሰራር መፃህፍቶች ተጠቅሷል። እንዲሁም በታላቋ ብሪጣንያ ሌሎች ዓይነቶች ተስፋፍተው ነበር።

በ1890 ዓመተ ምህረት ነው ለመጀመርያ ጊዜ ደረቅ የተጠበሰ ድንች በገበያ ለመሸጥ የቀረበው። ደረቅ የተጠበሰ ድንች በጣም በብዛት መመረትና መሸጥ የተጀመረው፣ በዛች ኣሰራሩን ባቃለለችው የድንች መጥበሻ መሳርያ በመፈጠሩ ነው። ይሄም የሆነው በ1920 ዓመተ ምህረት መጨረሻ ነው። በዚህ ቀጣይ ዓመታት ውስጥ ደግሞ የድንች ጥብስ ማሸግያው ተቀየረ፣ ደግሞም ደረቅ የተጠበሰ ድንች ሩቅ ቦታዎች በኣሜሪካ መሰራጨት ጀመረ። ኣውሮፓን በሚመለከት ደረቅ የተጠበሰ ድንች መስፋፋት እስከ 1950 ዓመተ ምህረት ዘግይቶ ነበር።

# ጥያቄዎች ስለ ”ደረቅ የድንች ጥብስ”

**ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት ኣድርግ። ኣንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።**

**1. ለምንድነው ደራሲው ይሄን ፅሁፍ የፃፈው?**

ሀ ☐ ኣንባቢውን ስለ የድንች ጥብስ ታሪክ ለማሳወቅ።
ለ ☐ ኣንባቢውን በዚህ ኣዝናኝ ታሪክ ለማስደሰት።
ሐ ☐ ኣንባቢውን የድንች ጥብስ እንዴት እንደሚሰራ ለማሳወቅ።

**2. የድንች ጥብስ ማን እንደፈጠረው ይታወቃል ወይ?**

ሀ ☐ ኣዎ፣ ጆርጅ ክሩም ነው።
ለ ☐ ኣይ፣ ብዙ ሌሎች ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል።
ሐ ☐ ኣይ፣ የት እንደተፈለሰፈ ግን ይታወቃል።

**የትኛው ኣረፍተነገር ነው ከደረቅ ድንች ጥብስ ፅሁፍ ጋር የሚስማማው? ኣዎ ወይም ኣይደለም የሚለው ላይ የX ምልክት ኣድርግ።**

| | | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|---|
| 3. | ከመቼ ጀምሮ ደረቅ የተጠበሰ ድንች ሊበላ እንደተጀመረ በግምት እናውቃለን። | ☐ | ☐ |
| 4. | ኣውሮፓ ለመጀመርያ ጊዜ የድንች ጥብስ የተሸጠባት ኣህጉር ነበረች። | ☐ | ☐ |
| 5. | ሰዎች በ1900 ክፍለ ዘመን ለምን ብዙ የድንች ጥብስ መብላት እንደጀመሩ ከኣንድ በላይ ምክንያቶች ኣሉ። | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

6. ስለዚህ ፅሁፍ ታሪክ ባጭሩ በራስህ ኣባባል ልትገልፅ ትችላለህ ወይ?



D. Harrison, Historiebloggen. www.svd.se (publicerad 2014-09-28) Bearbetad. Fotografi Pixabay.

# Textpaket 3



# ጊንጥ – የሸረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው

በሞቃታ ቦታዎች በሚገኙ ግድግዳዎች ውስጥ በሚፈጠር ትናንሽ ቀዳዳዎች እና ድንጋዮች መካከል ጣታችሁን መክተት ኣይመከርም። በተጨማሪም ባዶውን ለረጅም ጊዜ የቆየ ጫማ ማራገፍ ይገባል። ምናልባት ኣሁን ባዶውን ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም ጊንጦች ብርሃን ኣይወዱም። ስለዚህም ነው በቀዳዳና ጨለም ባሉ ቦታዎች ተጣብቀውና ተኝተው ቀኑን የሚያሳልፉት። ጊንጦች በመላው ዓለም በሞቃት ኣገሮች ይኖራሉ፡ ግን ብዙውን ጊዜ ኣይታዩም።

## ያደኑትን ነፍሳት ወግቶ መግደል

ጊንጦች በእርግጥ መርዛማ ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳን ኣብዛኛዎች ዝርያዎች ለኛ ለሰው ልጆች ለሞት የሚያበቁን ባይሆኑም፣ እነሱም እንደየ ዝርያቸው ቁመታቸው ከኣንድ እስከ ሃያ ሴንቲሜትር ይሆናሉ። ነገር ግን ሁሉም ጊንጦች መርዛማ የሆነ መንደፍያ ጭራቸው ጫፍ ላይ ኣላቸው። ኣንድ ጊንጥ ያደነውን ነፍሳት ለመግደል ሲል ጭራውን ወደ ጀርባው በማዞር ያንን ያደነውን ነፍሳት በጥፍሩ ኣጥብቆ ይዞ ይወጋዋል። ኣንድ የፈራ ጊንጥ መንደፍያውን ወደ ጠላቱ በማመልከት ዙርያውን በፍጥነት ይሽከረከራል።

ጊንጦች ትላልቅ ሸረሪቶችንና ሌሎች ትናንሽ ነፍሳቶችን በሌሊት ያድናሉ። እነሱም በጥፍራቸው በመዳሰስ ያደኑትን ነፍሳት ቀርቅረው በመያዝ በዛ መርዛማ መንደፍያቸው ኣድርገው ይገድሉታል።



*ጊንጥ*



K. Åström, *Boken om världen.* 2001. Fotografi Wikimedia Commons.

# ጥያቄዎች ስለ ”ጊንጥ – የሽረሪት ዝርያ ከነመንደፍያው”

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ኣዎ ወይም ኣይደለም በማለት መልስ።**

| | | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|---|
| **1.** | ጊንጦች ጨለማ ይወዳሉ? | ☐ | ☐ |
| **2.** | ሁሉም ጊንጦች ሰዎችን ሊገድሉ ይችላሉ? | ☐ | ☐ |
| **3.** | ሁሉም የጊንጥ ዝርያዎች እኩል ናቸው? | ☐ | ☐ |
| **4.** | ጊንጦች በጥፍራቸው ነው ወይ ያደኑትን የሚይዙት? | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

**5.** ጽሑፉን ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል ኣሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?

**6.** ከዚህ ስለ ጊንጦች ከተጻፈው ጽሑፍ ውስጥ ሰው ጫማውን ማራገፍ ኣለበት ይላል፡ ይሄ ለምን መደረግ ያለበት ይመስልሃል? ለምን እንደሱ እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ ወይ?

# ደረቅ የድንች ጥብስ



*ደረቅ የድንች ጥብስ*

ደረቅ የድንች ጥብስ በስስ ተከትፎ በዘይት ከተጠበሰ ድንች ሲሆን፣ ይሄም በ1800 ክፍለ ዘመን በጣም ከተወያዩበት ፈጠራዎች ኣንዱ ነው። ስለዚህም ለመጀመርያ ጊዜ ማን እንደፈጠረውና መቼ መሸጥ እንደተጀመረ ብዙ ታሪኮች ይወራሉ። ከነዚህ ታሪኮች ውስጥ እውነተኛ ይዞታ ያለውን ታሪክ ማግኘት ከባድ ሲሆን እንድያውም የማይቻል ነው።

ከዚህ ሁሉ በብዛት ከተወራው ታሪክ ስለ ምግብ ኣብሳዩ ጆርጅ ክሩም የተባለ ነበር። ነሓሴ 24 1853 ክሩም ለኣንድ ያልተደሰተ ደንበኛው ለማርካት ሞከረ። ስስ ኣድርጎ የቆራረጠውን ድንች በመጥበስ፣ ውጠቱ ላይ ደግሞ ጨው ነሰነሰበት፣ እንደ ውጤቱ ደግሞ ያ ደንበኛው ካለመደሰት ወደ በጣም የመደሰት ሁኔታ ተቀየረ። ይሄ ታሪክ ሃቀኛ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሌሎች ምግብ ኣብሳዮች በዚያ ዘመን ተመሳሳይ ሃሳብ ያስቡ እንደነበረ ሊታወቅ ተችሎኣል። በኣሜሪካ ብቻ በተመሳሳይ በኣንድ ሁለት የምግብ ኣሰራር መፃህፍቶች ተጠቅሷል። እንዲሁም በታላቋ ብሪጣንያ ሌሎች ዓይነቶች ተስፋፍተው ነበር።

በ1890 ዓመተ ምህረት ነው ለመጀመርያ ጊዜ ደረቅ የተጠበሰ ድንች በገበያ ለመሸጥ የቀረበው። ደረቅ የተጠበሰ ድንች በጣም በብዛት መመረትና መሸጥ የተጀመረው፣ በዛች ኣሰራሩን ባቃለለችው የድንች መጥበሻ መሳርያ በመፈጠሩ ነው። ይሄም የሆነው በ1920 ዓመተ ምህረት መጨረሻ ነው። በዚህ ቀጣይ ዓመታት ውስጥ ደግሞ የድንች ጥብስ ማሸግያው ተቀየረ፣ ደግሞም ደረቅ የተጠበሰ ድንች ሩቅ ቦታዎች በኣሜሪካ መሰራጨት ጀመረ። ኣውሮፓን በሚመለከት ደረቅ የተጠበሰ ድንች መስፋፋት እስከ 1950 ዓመተ ምህረት ዘግይቶ ነበር።

# ጥያቄዎች ስለ ”ደረቅ የድንች ጥብስ”

**ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት ኣድርግ። ኣንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።**

1. **ለምንድነው ደራሲው ይሄን ፅሁፍ የፃፈው?**

ሀ ☐ ኣንባቢውን ስለ የድንች ጥብስ ታሪክ ለማሳወቅ።
ለ ☐ ኣንባቢውን በዚህ ኣዝናኝ ታሪክ ለማስደሰት።
ሐ ☐ ኣንባቢውን የድንች ጥብስ እንዴት እንደሚሰራ ለማሳወቅ።

2. **የድንች ጥብስ ማን እንደፈጠረው ይታወቃል ወይ?**

ሀ ☐ ኣዎ፣ ጆርጅ ክሩም ነው።
ለ ☐ ኣይ፣ ብዙ ሌሎች ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል።
ሐ ☐ ኣይ፣ የት እንደተፈለሰፈ ግን ይታወቃል።

**የትኛው ኣረፍተነገር ነው ከደረቅ ድንች ጥብስ ፅሁፍ ጋር የሚስማማው? ኣዎ ወይም ኣይደለም የሚለው ላይ የX ምልክት ኣድርግ።**

| | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|
| 3. ከመቼ ጀምሮ ደረቅ የተጠበሰ ድንች ሊበላ እንደተጀመረ በግምት እናውቃለን። | ☐ | ☐ |
| 4. ኣውሮፓ ለመጀመርያ ጊዜ የድንች ጥብስ የተሸጠባት ኣህጉር ነበረች። | ☐ | ☐ |
| 5. ሰዎች በ1900 ክፍለ ዘመን ለምን ብዙ የድንች ጥብስ መብላት እንደጀመሩ ከኣንድ በላይ ምክንያቶች ኣሉ። | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

6. ስለዚህ ፅሁፍ ታሪክ ባጭሩ በራስህ ኣባባል ልትገልፅ ትችላለህ ወይ?



D. Harrison, Historiebloggen. www.svd.se (publicerad 2014-09-28) Bearbetad. Fotografi Pixabay.

# እንቅልፍ።

***ሁሉም ፍጥረታት እንቅልፍ ያስፈልጋቸዋል፣ የሰው ልጅ ሆነ እንስሳትም። ግን ለምንድን ነው? ተመራማሪዎችም እንኳን መልሱን ኣያውቁትም። እንዲሁም በእንቅልፋችን ጊዜ ምን አንደሚከናወን ተመራማሪዎች እስከ ኣሁን የደረሱበት ነገር የለም። እንቅልፍ እንደሚያስፈልገን ግን ጥርጥር የለውም። ካለ እንቅልፍ በሂይወት መኖር ኣንችልም።***

ከእረፍት ኣይነቶች ኣንዱ እንቅልፍ ነው። ይሁን እንጂ በምትተኛበት ጊዜ በኣከባቢህ ምን እየተከናወነ እንዳለ ማወቅ ኣትችልም። በሌላ ኣነጋገር ስትተኛ ሁለንትናህ ኣይታውቅህም ማለት ነው። ነግር ግን ከቀሰቅሱህ በቀላሉ ከመነሳት የሚያግድህ ነገር የለም።


## የእንቅልፉ ዑደት።

እንቅልፍ ተደጋጋሚ ዑደት ያደርጋል፣ እያንዳዱ ዑድት ደግሞ 90 ደቂቃዎች ያህል ይፈጃል። እያንዳንዱ የእንቅልፍ ዑደት ደግሞ ኣምስት ደረጃዎች ኣሉት። ስል እንቅልፍ ዑደት ስእሉን ተመልከት።

## የህልም- እንቅልፍ እና ከባድ- እንቅልፍ።

ኣምስተኛው ደረጃ፣ የህልም-እንቅልፍ ይባላል። በዚሁ ደረጃ ውስጥ ኣይኖች በፍጥነት ይርገበገባሉ። የዛኔ ነው ህልም ውስጥ ያለነው። የህልም-እንቅልፍ በጥልቀት የምንተኛው ኣይደለም፣ ይሄም ማለት ጥሩ እንቅልፍ ኣይደለም ማለት ነው። የህልም እንቅልፍ በየ 90 ደቂቃዎቹ ውስጥ ተደጋጋሚ ዑደት ያደርጋል። ይህም ማለት ከጠቅላላ የእንቅልፍ ጊዜያችን ውስጥ ኣንድ ኣራተኛውን ያህል ጊዜ የህልም- እንቅልፍ ሂደት ነው። ሌላኛው ደረጃ ከባዱ- እንቅልፍ ነው። በዚህ ጊዜ ሰውነታችን እንደገና ይታደሳል፣ በተጨማሪም ኣዳዲስ ነገሮች የመማር ችሎታችን የተሻለ ይሆናል። በዚህ የከባድ-እንቅልፍ ጊዜ ውስጥ እውቀታችን ይጨምራል፣ ብቀላሉ ደግሞ ኣእምሯችን ውስጥ በመስፈር የማስታወስ ችሎታችን ከፍ ይላል።

**የእንቅልፍ ዑደት**




## እንቅልፍ መተካት።

ኣንድ ቀን ኣምሽተህ ከተኛህ፣ ለንጋታው በእጥፍ እተኛለሁ ብለህ ማሰብ በጣም ቀላል ነው። ነገር ግን ትክክል ኣይደለም። ሰውነታችን ያለፈብንን እንቅልፍ ጥሩ የመተካት ችሎታ ኣለው። በቂ እንቅልፍ ካልተኛህ እንደገና ከባድ እንቅልፍ በመተኛት የባከነውን እንቅልፍ መተካት ይቻላል።



H. Borgström, *Kroppens mysterier.* 2010. Bearbetad. Figur G. Wallentin.

# ጥያቄዎች ስለ "እንቅልፍ"

**የትኛው ኣባባል ነው ስለ እንቅልፍ ከተፃፈው ፅሁፍ ጋር የሚስማማው? ለያንዳንዱ ኣባባል ኣዎ ወይም ኣይደለም የሚለው ላይ የ X ምልክት ኣድርግ።**

| | | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|---|
| 1. | የሰው ልጅ ለምን እንቅልፍ እንደሚኣስፈልገው ተመራማሪዎቹ ያውቃሉ። | ☐ | ☐ |
| 2. | በህልም-እንቅልፍ ጊዜ ውስጥ ሰው ከባድ ያልሆነ እንቅልፍ ይተኛል። | ☐ | ☐ |
| 3. | ለሊቱን በሙሉ ስንተኛ ኣብዛኛው ህልም ነው። | ☐ | ☐ |
| 4 | ከህልም- እንቅልፍ ብኋላ ከመቀስቅስ ከህልም-እንቅልፍ በፊት መቀስቀስ ይቀላል። | ☐ | ☐ |

**ትክክለኛ መልስ ነው ያልከውን የ x ምልክት በማድረግ ኣረፍተነገሩ ላይ ቀጥልበት። ካሉት ምርጫዎች ውስጥ ምልክት ማድረግ የሚቻለው ኣንድ ጊዜ ብቻ ነው።**

5 ኣንድ ሰው ለኣንድ ወይም ለሁለት ሌሊት ያህል በቂ እንቅልፍ ያልተኛ እንደሆን – --
– – – -- – – --።

ሀ ☐ ያለፈበትን እንቅልፍ ለመተካት እጥፍ ጊዜ ለሚቀጥለው ሌሊት መተኛት ያስፈልገዋል።
ለ ☐ ለሚቀጥለው ሌሊት ከባድ- እንቅልፍ በመተኛት ሰውነታችን ያጠፋውን ሃይል መተካት ይችላል።
ሐ ☐ ያልተኛውን እንቅልፍ ለመተካት በማግስቱ ኣስቀድሞ መተኛት ኣለበት።

**ቀጣዩን ጥያቄ በቃል መልስ።**

6 ስለዚህ ፅሁፍ ታሪክ ባጭሩ በራስህ ኣባባል ልትገልፅ ትችላለህ ወይ?



H. Borgström, *Kroppens mysterier.* 2010. Bearbetad. Figur G. Wallentin.

# ወተት

## ለጋዜጣ አዘጋጆች የተፃፈ ደብዳቤ

በስዊደን ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምሳ ይሰጣቸዋል፣ ከምሳ ጋርም ብዙውን ጊዜ ወተት ይቀርባል፡፡ በዚህ ባለፉት ጊዜያቶች ስለ ወተት መጠጣት በርግጥ ምን ጥቅም እንዳለው ሰዎች መወያየት ጀምረዋል፡፡ ስለ ወተት በትምህርት ቤት ማቅረብ ስለሚል ሁለት የተለያዩ ሰዎች ያላቸውን አስተያየት ከዚህ በታች ታነባለህ፡፡

1.

### ለተማሪዎች በወተት ፋንታ ውኃ ስጧቸው

**የላም ወተት በትምህርት ቤት ተፈጥሯአዎ አይደለም፡፡ በዚህ ምድር ላይ የሰው ልጅ ብቻ ነው የሌላ ዓይነት ዘር ወተት ተጠቃሚ፡፡**

**ባለፈው** ረቡዕ ጋዜጣ ላይ እንዳነበብነው አንድ ሰፊ ጥናት የተደረገበት በኡፕላሳ ዩንቨርስቲ ያ ያረጀና ያልተነቀፈ ስለ ላም ወተት አመለካከታችንን አዛብቶታል፡፡ ተመራማሪዎች ወተት በብዛት መጠጣት ዕድሜን የሚያሳጥርና ከአጥንት ስብራት ጋር የተያያዘ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

**የላም ወተት** ለሰው ልጆች ጤና እና ለአከቢያችን ተፈጥሮአዊም ወይም ደግሞ ጥሩም አይደለም፡፡ ስለዚህም፣ አሁንኑ የላም ወተትን ከስዊዲን ትምህርት ቤት አስወግደን በሱ ፋንታ ደግሞ ልጆችን አዲስ ያጠጣጥ ልማድ ለአከባቢያችንም የሚሻለውን ማስተማር ነው፡፡ እሱም ጥምን በውኃ ማርካት ነው፡፡

**አንደሽ ስቨንሶን**
የአታክልት ብሉ ማህበር ተወካይ

2.

### ወተት በትምህርት ቤት ከምግብ ጋር ያስፈልጋል

ለአንደሽ ስቨንሶን የተሰጠ መልስ

**አንደሽ ስቨንሶን ልጆች በትምህርት ቤት ወተት እንዲሰጣቸው አይፈልግም፡፡ እኛና የተባበሩት መንግስታት ተቃራኒ አመለካከታት አለን፣ ሁሉም ልጆች በትምህርት ቤት ወተት በነፃ ይገባቸዋል፡፡**

**ወተት** 18 ከ22ቱ ለኛ በየቀኑ ጠቃሚ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች የያዘ ሆኖ፣ ልጆች በትምህርት ቤት ውሎኣቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ የምግብ እጥረት ባለባቸው አገሮች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚቀርበው ወተት ለብዙ ልጆች ለሕይወታቸው ወሳኝ የሆነ የምግብ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም አዲስ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ልጆች ከምግብ ጋር ወተት ካልተሰጣቸው ያ የትምህርት ቤት ምሳ በቂ ንጥረ ነገር እንደማይኖረው አሳውቀዋል፡፡

ስለ ንጥረ ምግብ ይዘት ተማራማሪ የሆነችው ኡላ ሮሳንደር በክርስትያንሳታድ ኮለጅ በስዊድን በአንድ ከተማ ከሚገኙት ሶስቱ ትምህርት ቤቶች ዕድሜያቸው በአስር ዓመት ውስጥ ለሚገኙ ልጆች ለአንድ ሳምንት በትምህርት ቤት የሚበሉትን ምግብ ይዘት አጥንታለች፡፡ ትምህርት ቤቴቹም አንድ ዓይነት ምግብ አቅርበው ነበር፡፡ ውጤቱም እንዳሳየው ልጆች ከምግብ ጋር ወተት መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል፡፡ በጣም አስፈላጊ የሆነው ደግሞ አነስ ያለ መጠን ለሚበሉ ልጆችና ወይም ደግሞ በምሳ እረፍታቸው በቂ ምግብ ለመብላት ለማይደርሱ ልጆች ነው፡፡ ወተት የሚያስፈልገው ልጆች በቂ የሆነ እንደ ካልስየም፣ ቪታሚን ቤ12 እና ማግነዚየም እንዲያገኙ ነው፡፡ ለዚህም ነው ወተት በትምህርት ቤት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው፡፡

**ፔትራ ስትራንድበርይ**
የስዊዲን ወተት አምራቾች ተወካይ



J. Paulsson & J. Carlberg, Insändare. *Upsala Nya Tidning*. Publicerade 2014-11-04 och 2014-11-11. (Bearbetade)

# ጥያቄዎች "ለጋዜጣ ኣዘጋጆች ስለ ወተት የተፃፈ ደብዳቤ"

**ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት ኣድርግ። ኣንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።**

1. ስትራንድበርይ ለምንድ ነው በትምህርት ቤት ወተት መስጠት አስፈላጊ ነው ብላ የምታምነው?

ሀ ☐ ወተት ልጆችን በትምህርት ቤት ውስጥ ብዙ እንዲበሉ ያደርጋል

ለ ☐ ወተት የሰውን ዕድሜ ያረዝማል

ሐ ☐ ወተት ብዙ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ነው

2. ለምንድነው ስቨንሰን ተማሪዎች ከወተት ይልቅ ውሃ መጠጣት እንዳለባቸው የሚያምነው?

ሀ ☐ ውሃ ከወተት ይልቅ ርካሽ ነው

ለ ☐ ውሃ ለአካባቢ ተስማሚ ነው

ሐ ☐ ውሃ ጥምን በይበልጥ ስለሚያረካ

3. በፅሁፉ መሰረት ምርምሩ ምን ኣሳይቶኣል?

ሀ ☐ ወተት መጠጣት ጠቃሚና ጎጂ ጎኖች እንዳሉት

ለ ☐ በትምህርት ቤት የሚሰጠው ምግብ ካለ ወተት በቂ ንጥረ ነገር ስላለው

ሐ ☐ ወተት በብዛት መጠጣት ጠንካራ አጥንቶች ስለሚሰጥ

4. ለምንድነው ስትራንድበርግ ለጋዜጣ የፃፈችው?

ሀ ☐ እሷ ስቨንሶን ለምን እንደተሳሳተ ልትገልጽ ስለፈለገች

ለ ☐ እሷ ውሃ ለአካባቢ ጥሩ እነደሆነ ለማስረዳት ስለፈለገች

ሐ ☐ እሷ ልጆች በትምህርት ቤት ውስጥ ትንሽ ምግብ እንዲመገቡ ስለማትፈልግ

**የትኛው ኣባባል ነው ስለ ወተት ከተፃፈው ፅሁፍ ጋር የሚስማማው? ለያንዳንዱ ኣባባል ኣዎ ወይም ኣይደለም የሚለው ላይ የ X ምልክት ኣድርግ።**

| | ኣዎ | ኣይደለም |
|---|---|---|
| 5. ስቨንሶን ሰው ብዙ ወተት ከጠጣ ዕድሜው ኣጭር ይሆናል ይላል | ☐ | ☐ |
| 6. ስቨንሶንና ስትራንድበርይ በፅሁፋቸው ሁለቱም ኣንድ ተማራማሪ ይጠቅሳሉ | ☐ | ☐ |
| 7. ተማራማሪዎቹ ስለ ወተት ውጤቶች የጋራ ኣስተሳሰብ ያላቸው ይመስላል | ☐ | ☐ |

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።**

8. ስለዚህ ፅሁፍ ታሪክ ባጭሩ በራስህ ኣባባል ልትገልፅ ትችላለህ ወይ?

9. የትኛው ፅሁፍ ነው በይበልጥ ያሳመነህ? ለምን እንደሱ እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ ወይ?

# የአለም ከተሞች በፍጥነት በማደግ ላይ ናቸው ።

የአለም  የከተሞች እድገት በፍጥነት እየጨመረ ነው። እንደ ተባበሩት መንግስታት ጥናት መሰረት እስከ 2050 ዓ. ም ድረስ የከተሞች ህዝብ ብዛት እስከ 2,4 ቢልዮን ሊያድጉ ይጠበቃል። እናም ሁላችንንም ቦታ እንድናገኝ  ከተሞቹ በተመሳሳይ እንደ ህንድ አገር  መስፋት ይኖርባቸዋል።

በ 1900 ክፍለ ዘመን በአለም በከተማዎች ውስጥ የሚኖር የህዝብ ብዛት ከ220 ሚልዮን  ወደ 2,8 ቢሊዮን ከፍ ብለዋል።  እንደ ተባበሩት መንግስታት ጥናት መሰረት በ2008 ዓ.ም  ለመጀመሪያ ጊዜ ከተሞች ውስጥ  የሚኖር የህዝብ ብዛት ከገጠሩ ህዝብ የበዛ ነበር።


በ2013 ዓ. ም በከተማዎች ውስጥ የሚኖረው የአለም ህዝብ ብዛት ወደ 3,6 ቢሊዮን  እንደሚደርስ ተገምተዋል፣ ነገር ግን እንደ ተባበሩት መንግስታት ትንበያ መሰረት እስከ  2030 ዓ.ም  ብዛቱ  በ 5 ቢሊዮን ከፍ ይላል፣ በ2050 ዓ.ም ደግሞ ቁጥሩ ከ6 ቢሊዮን በላይ ያልፋል። በአውሮፓ፣ በሰሜንና ደቡብ አመሪካ አብዛኛዎቹ  ህዝቦች ቀድመው በከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ በአፍሪቃ እና በኤስያ ግን  የከተሞቹ  የህዝብ ቁጥር አሳሳቢ የሆነ እድገት ይጠብቃቸዋል።

**በማደግ ላይ የሚግኙ ከተሞች፣  ችግርና  መፍትሄ።**

በእድገት ላይ የሚገኙ ከተማዎች በብዙ መንገድ ከባድ ችግር  ኣላባቸው፣ ምክንያቱ በፍጥነት የሚያድጉ ከተማዎች የአከባቢና  የጤንነት ችግር ያመጣሉ። ለምሳሌ ያህል የአየር ብከላ እና ያአከባቢ  ጽዳት። ይህ እንደዚህ እንዳለ  በእድገት ላይ የሚገኙ ትላልቅ  ከተማዎች፣ በገጠሮች ውስጥ የማይግኙ፣ ብዙ ምርጫዎች ማሟላት ይችላሉ፣ ለምሳሌ ህክምና፣ ትምህርት እንዲሁም የስራ እድሎች።.

ብዙ ህዝቦች  ኣንድ ላይ ተቀራርበው  ሲኖሩ፣ የነዳጅ እና መጓጓዣ  ተፈላጊነቱ  ሊቀንስ  ይችላል። ይሄ ደግሞ በአየር ብከላ ላይ የሚፈጥረውን  ጫና  ይቀንሳል።

**የአለም ህዝብ እድገት ከ 1961--2012  እና  የአለም ህዝብ እድገት ትምበያ ከ2013-2050**





J. Moström, *www.scb.se* (publicerad 2013-10-10)

# ጥያቄዎች ”የአለም ከተሞች በፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛሉ”።

ትክክለኛ ነው ብለህ ያመንክበትን መልስ የX ምልክት አድርግ። አንድ ምልክት ብቻ ነው የሚፈቀደው።

1. እንደ ጽሁፉ መሰረት፣ ሰዎች ገጠሩን ትተው ከተማዎች ውስጥ ሲገቡ ፣ዋናው ጉዳት የትኛው ነው?

ሀ ☐ የከተማዎች አከባቢ ይበላሻል።

ለ ☐ ከተማዎች ይሰፋሉ።

ሐ ☐ የመጓጓዣ ተፈላጊነት ይጨምራል።

2. በ2040 ዓ . ም. ከተማዎች ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ህዝቦች ቁጥራቸው በግምት ስንት ይደርሳል?

ሀ ☐ 6,4 ቢሊዮን።

ለ ☐ 3,6 ቢሊዮን።

ሐ ☐ 5,7 ቢሊዮን።

3. እንደ ጽሁፉ መሰረት ፣ የከተማ ነዋሪዎች ቁጥር ለመጨመር ትልቁ ምክንያት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ ☐ ከተማዎች ከሌላ የተሻሉንና ምቹም ናቸው።

ለ ☐ ከተማዎች ውሳጥ ኑሮ የተሻለ ነው ።

ሐ ☐ ከተማዎች ውስጥ በቀላሉ መንቀሳቀስ ይቻላል።

4. በ1961 ዓ. ም በከተማና በገጠር ውስጥ ይኖር የነበረው የአለም ህዝብ ከብዛቱ አኳያ ሲታይ እንዴት ይኖር ነበር?

ሀ ☐ ከከተማ ኑዋሪዎች ይበልጥ በእጥፍ የሚቆጠር ህዝብ ገጠር ውስጥ ይኖር ነበር።

ለ ☐ የከተማ ኑዋሪዎች ብዛት ከገጠሩ ኑዋሪዎች ይበልጥ ነበር።

ሐ ☐ ከተማና ገጠር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ብዛታቸው እኩል ነበር።

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃልህ መልስ።

5. ጽሑፉን ስለምን እንደተጻፈ በራስህ ቃል ኣሳጥረህ ልትገልጽ ትችላለህ?

6. ጽሁፉ እንደየሚገልጸው ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ቁጥር እየጨመረ ነው።I በከተማ ከመኖር ይልቅ በገጠር ውስጥ መኖር ያሉት ጥቅሞች የትኞቹ ናቸው? ለምን እንደሱ እንዳሰብክ ልትገልጽ ትችላለህ ወይ?

## Litteraturförteckning


Aisopos. Den girige. I: *Aisopos' fabler*. Ny översättning av Erik Hedén med illustrationer av Arthur Rackham. 1919. Stockholm: Svenska andelsförlaget. (bearbetad)

Aronsson, Karin & Stellan Ottosson, 1993. Lejonet och räven. I: K. Aronsson & S. Ottosson; illustrationer I-K Eriksson & M. Korotyńska, *Min läsebok Blå rosen*. 2:a uppl. Stockholm: Liber. (bearbetad)

Borgström, Håkan, 2010. Sover kroppen när du sover? I: H. Borgström. 2010. *Kroppens mysterier*. Enskede: Borgströms Förlag. (bearbetad)

Carlberg, Jonas, 2014. Mjölken behövs till skolmaten. *Upsala Nya tidning*. Insändare. Publicerad 2014-11-11. (bearbetad)

*En karta över en ö*. Kartan och frågorna anpassade från IEA Reading Literacy Study. © 1990. International Association for the Evaluation of Educational Achievement (IEA). The Hague: International Association for the Evaluation of Educational Achievement (IEA), IEA Secretariat[1].

Harrison, Dick, 2014. Hur länge har vi ätit potatischips? Historiebloggen. *Svenska Dagbladet* http://blog.svd.se/historia/2014/09/28/hur-lange-har-vi-atit-potatischips/?fromMobile=true Publicerad 2014-09-28. Hämtad 2014-10-19. (bearbetad)

Moström, Jerker, 2013. Världens städer växer allt snabbare. SCB. Statistiska centralbyrån. http://www.scb.se/sv_/Hitta-statistik/Artiklar/Varldens-stader-vaxer-allt-snabbare/# Publicerad 2013-10-10. Hämtad 2015-01-08. (utdrag)

Paulsson, Jonas, 2014. Ge barnen havremjölk i stället. *Upsala Nya Tidning*. Insändare. Publicerad 2014-11-04. (bearbetad)

Åström, Karin, 2001. Skorpionen – ett spindeldjur med gadd. I: S. Andersson, K. Åström & S. Rune. *Boken om världen*. Stockholm: Liber. (Utdrag)


## Bildförteckning


Lejonet och räven. Eriksson, Inga-Karin, 1993. I: K. Aronsson & S. Ottosson; illustrationer I-K Eriksson & M. Korotyńska, *Min läsebok Blå rosen*. 2. uppl. Stockholm: Liber.

Fotografi på skorpion. Hämtad 2015-06-24 https://upload.wikimedia.org/wikipedia/commons/6/6d/Emperor_scorpion_or_Imperial_scorpion_(Pandinus_imperator).jpg

Fotografi på potatischips. Hämtad 2015-02-03 https://pixabay.com/p-476359/?no_redirect


[1] Att IEAs skrifter, studiematerial och undersökningar med organisationens tillstånd får användas för forsknings- och utbildningsändamål ska inte tolkas som att IEA medverkat i eller godkänt någon del av forskningen, eller rapporteringen kring den, eller de utbildningsprogram vari materialet används.